## 4. የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ የጊዜ ገደብ ምን ያህል ነው?

- ልደት በተከሰተ በ90 ቀናት ውስጥ መመዝገብ አለበት፡፤
- የጋብቻ፤ የፍቺና የሞት ኩነቶች በተከሰቱ በ30 ቀናት ውስጥ መመዝገብ ይኖርባቸዋል።

## 5. ወሳኝ ኩነቶችን የሚያስመዘግቡ አካላት ማን ማን ናቸው?

### 5.1 የልደት ኩነት አስመዝጋቢ አካላት

- የህጻኑ ወላጆች፤ ወላጆቹ የሌሉ እንደሆነ አሳዳሪዎች ወይም ህጻኑን በመንከባከብ ላይ ያለ ሰው የህጻኑን ልደት ማስመዝገብ ግዴታ አለበት፤

### 5.2 የጋብቻ ኩነት አስመዝጋቢ አካላት

- ጋብቻው የተፈጸመው በክብር መዝገብ ሹም ፊት ከሆነ የክብር መዝገብ ሹሙ ጋብቻውን ወዲያውኑ መመዝገብ አለበት።
- ጋብቻው በሃይማኖታዊ ወይም በባህላዊ ስርአት የተፈጸመ እንደሆነ ተጋቢዎች በአዋጁ ላይ የተመለከተውን ማስረጃ (የተጋቢዎች ስም፤እድሜ ፤ መደበኛ መኖሪያ ቦታ፤ጋብቻው የተፈጸመበት ቀንና ቦታ እና የምስክሮች ስምና መደበኛ ቦታ) የሚገልጽ ማስረጃ ለክብር መዝገብ ሹም አቅርበው ጋብቻውን ማስመዝገብ አለባቸው።

### 5.3 የፍቺ ኩነት አስመዝጋቢ አካላት

- ተፋቺዎች በጋራ ወይም ከተፋቺዎች አንዱ ስልጣን ባለው ፍ/ቤት የተወሰነ የፍቺ ውሳኔን ለክብር መዝገብ ሹሙ በማቅረብ ፍቺውን ማስመዝገብ አለባቸው፤

### 5.4 የሞትን ኩነት አስመዝጋቢ አካላት

- ከሟች ጋር አብሮ ይኖር የነበረ ሰው፤ አብሮ ይኖር የነበረ ሰው የሌለ እንደሆነ የሟች የስጋ ወይም የጋብቻ ዘመዶች እነዚህ የሌሉ እንደሆነ የቅርብ ጎረቤት ወይም ስለሟቹ መሞት የሚያውቅ ማንኛውም ሰው ሟች መሞቱን ማስመዝገብ አለበት።
- በአደጋ ወይም ባልታወቀ ምክንያት ሞቶ ማንነቱ ስላልታወቀ አስክሬን ሪፖርት የተቀበለ ፖሊስ ሪፖርቱ ከደረሰው ቀን በኋላ ባሉት ሦስት ቀናት ውስጥ ሞቱን ማስመዝገብ አለበት።
- ሞቱ የተከሰተው በአዳሪ ትምህርት ቤት ወይም በሌላ የጋራ መኖሪያ ስፍራ የሆነ እንደሆነ የተቋሙ ሃላፊ ሞቱን ማስመዝገብ አለበት።
- ሞቱ የተከሰተዉ በጤና ተቋም ዉስጥ ከሆነ ወይም አስክሬን ለምርመራ ወደ ጤና ተቋሙ የመጣ እንደሆነ ተቋሙ የሟችን ስም፣ ጾታ እና የትዉልድ ቀን፣ የሞተበትን ቀን፤ ቦታ እና የሞቱን ምክንያት እና የመሳሰሉ መረጃዎችን የያዙ የሞት ማሳወቂያ ቅጽ ወዲያዉኑ ሞልቶ ሞቱን የማስመዝገብ ግዴታ ላለበት ሰዉ መስጠት አለበት፣
- ሞቱ የተከሰተዉ ከጤና ተቋም ውጪ የሆነ እንደሆነ በዝቅተኛው አስተዳደር እርከን ላይ ያለው የጤና መዋቅር ወይም የጤና ባለሙያ አግባብነት ያላቸው መረጃዎችን የያዘ ማሳወቂያ ቅፅ ወዲያውኑ ሞልቶ ሞቱ የተከሰተበት ቦታ ለሚገኝ አስተዳደር ጽ/ቤት ማሳወቅ አለበት።



## 6. የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ምን ምን መርሆችን አሉት?

### 1) ያለማቋረጥ /continuity/፡-

- በየቀኑ፣ በየወሩ ፣ በየዓመቱ፣ በየዓመታቱ ዘመን ተሻጋሪ ለትውልድ የሚሻገር የወሳኝ ኩነት መረጃዎችን ለማስገኘት የሚያስችል የምዝገባ ተግባር ነው። ይህን መሰረት በማድረግ በአሁኑ ሰአት ምንም እንኳን የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ አለምን ያስጨነቀ ቢሆንም የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ፅ/ቤቶች እራሳቸውን እና ተገልጋዩን ህብረተሰብ ለቫይረሱ በማያጋልጥ ሁኔታ የኩነት ምዝገባ ስራን ባለማቋረጥ በማከናወን ላይ ይገኛሉ።

### 2) ቋሚነት /permanence/፡-

- የሰዎች መወለድ ፣ መጋባት ፣ መፋታት፣ መሞት የማያቋርጡ ክስተቶች እንደመሆናቸው መጠን የምዝገባ ስርዓቱም በቋሚነት በተቋቋመ ተቋም/መሥሪያ ቤት የሚከናወን ተግባር ነው ፣

### 3) አስገዳጅነት /compulsoriness/፣-

- የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ስርዓት ግለሰብና ቤተሰብን፣ አልፎም ህብረተሰብን የሚመለከት በመሆኑ በማህበረሰብ ህግ ይካተታል። በተጨማሪም የምዝገባ ስረአቱ ወጥነት ያለው አስተዳደር እንዲኖረው ለማስቻል የህግ ወሰን ያለው አስገዳጅነት ሊኖረው ይገባል።

### 4) ሁሉን አቀፍ /universality/

- ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል፤ ቤተሰብ ፣ ማህበረሰብ ፣ ጎሳ፣ ዘር ፣ ሃይማኖት የሚያካትት ነው።
- በተራራ፣ በአየር ፀባይ ፣ በወንዝ የማይገደብ እንዲሁም
- ከጎጥ፣ መንደርና ቀበሌ ጀምሮ የአንድን ሀገር ሙሉ የአስተዳደር ክልል አጠቃሎ በምዝገባው ማካተትን የግድ የሚል የምዝገባ ስርዓት ነው ።

ያግኙን

Website: - WWW.invea.gov.et

Facebook: - FDRE Immigration Nationality and Vital Events Agency

Tel:- +251111719223 / +251111569914



INVEA®

የኢሚግሬሽን ፤ ዜግነትና የወሳኝ ኩነት ኤጀንሲ

IMMIGRATION NATIONALITY & VITAL EVENTS AGENCY

# ኢሚግሬሽን፤ ዜግነትና ወሳኝ ኩነት ኤጀንሲ

## በአገር አቀፍ ደረጃ ለ3ኛ ጊዜ የሚከበረው የወሳኝ ኩነት ምዝገባ እና ስታቲስቲክስ ቀን

**የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ ተፅዕኖን በመቋቋም የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ስርዓት ቀጣይነት ይረጋገጣል!**

ነሀሴ 4 / 2012 ዓ.ም

## 1. የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ጽንሰ-ሃሳብ

### ★ ወሳኝ ኩነቶች የሚባሉት ምን ምን ናቸው?

የተለያዩ ሃገራት እንደየህጋቸው ሁኔታ የተለያዩ በሰው ልጅ ህይወት ውስጥ የሚከሰቱ ኩነቶችን ወሳኝ ኩነት ብለው ይመዘግባሉ። በኢትዮጲያ ወሳኝ ኩነት ተብለው የሚመዘገቡት ልደት ፣ ሞት ፣ጋብቻ፣ ፍቺ ፤ ጉዲፈቻ ፣ ልጅነትን መቀበል እና አባትነትን በፍርድ ቤት ማወቅ ናቸው።

### ★ ወሳኝ ኩነት ምዝገባ ወሳኝ የተባሉበት መሰረታዊ ምክንያት ምንድን ነው?

- በሃገራት ህገ-መንግስት እና በተለያዩ ዓለም አቀፍ ድንጋጌዎች የታወቁ መሰረታዊ የሰብአዊ ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ መብቶችን ለመጠበቅ ዋነኛ የመረጃ ምንጭ እና ግብዓት በመሆናቸው፣
- ግለሰቦችን ከመንግስት ጋር በማገናኘት የማንነት መነሻ ህጋዊ መረጃዎች በመሆናቸው እና የአንድን ሀገር ህዝብ ብዛትና ዕድገት የሚወስኑ ፣ ለህብረተሰቡ አልፎም ለግለሰቦች ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አገልግሎቶችን ለመስጠት የሚዘጋጁ ፖሊሲዎች እና ፕሮግራሞችን በመቅረጽ ፣ዕቅዶችን በማዘጋጀት ፣ አፈጻጸማቸውን በመከታተልና በመገምገም ወሳኝ የሥነ-ህዝብ እና ጤና መረጃዎች በመሆናቸው፣
- ልደትና ሞት በሰው ልጅ ላይ አንድ ጊዜ የሚከሰቱ ተፈጥሮአዊ ክስተቶች ናቸው ። ስለሆነም ልደት በዚች ምድር የሰዎች የመኖር ህጋዊ መብት ምንጭ ኩነት በመሆኑ ማንኛውም ሰው በአንድ በታወቀ የአስተዳደር ክልል ለመኖር ህጋዊ የዜግነትና ማንነት መብት የሚያገኝበትና ለዚህም ማረጋገጫ የሚሆነውን ህጋዊ ሰነድ በመንግስት የሚዘጋጅበት የህይወቱ የመብት መነሻ እርከን በመሆኑ እንዲሁም ሞት የዚህ መብት መጨረሻ ወይም መቆሚያ እርከን በመሆኑ፣
- ጋብቻና ፍቺ ማንኛውም ሰው "ህጋዊ ሰው" የመሆን መብት በሚያገኝበትና በሚያጣበት የማህበረሰባዊ አኗኗር ሥርዓት ውስጥ የሚከሰቱ ዋነኛ የሰዎች ማህበረሰባዊና ህጋዊ የአቋም ለውጥ ጠቋሚ ወሳኝ ኩነቶች ናቸው። እነዚህ በግለሰቦች ላይ የሚከሰቱ ተፈጥሮአዊና ማህበረሰባዊ ለውጦች የአንድን ሀገር የህዝብ አስተዳደር በስርዓት ለመምራት መነሻ መሰረቶች በመሆናቸው ወሳኝ ኩነቶች ይባላሉ።



## 2.የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ዋና ዋና ጠቀሜታዎች ምንድን ናቸው?

### 2.1 የልደት ምዝገባ ጠቀሜታ፣

- የማንነት ህጋዊ መሰረት ለመጣል፣
- ወላጆችን ለማወቅ፤
- ቤተሰባዊ ዝምድና ለማወቅ፤
- የአሳዳጊን ማንነት ለመለየት፤
- የመታወቅ ህጋዊ መብትን ለማረጋገጥ

### ★ ዕድሜን መሠረት በማድረግ የተወሰነ ዕድሜ ሲደረስ የሚሰጡ የአገልግሎት መብቶችን ለመጠየቅ፡-

- ት/ቤት የመግባት ፍቃድ ለማግኘት፣
- በሥራ ለመሠማራት (ስራ የመቀጠር) ፈቃድ ለማግኘት፣
- የመውረስ እና ንብረት የማስተዳደር መብቶችን ለማግኛት፤
- በሰራዊት አባልነት ለማገልገል ወይም ከአባልነት ለመገለል፣
- የነዋሪነት ወይም የማንነት መታወቂያ ለመጠየቅ፣
- የመምረጥና መመረጥ መብትን ለመጠቀም፣
- ከካለእድሜ ጋብቻ ለመጠበቅ፣
- የህጻናት ጉልበት ብዝበዛ ለመከላከል፣

### 2.2 የሞት ኩነት ምዝገባ ጠቀሜታዎች

- ለሟች ቀሪ ዘመዶች ሟቹ ለመሞቱ ህጋዊ መረጃ ለመሆን፡-
- ውርስ የሚገባቸው የመውረስ ጥያቄ ለማቅረብ፣
- የኢንሹራንስ ጥያቄ ለማቅረብ፣
- የቤተሰብ ድጎማ ጥያቄ ለማቅረብ፣
- በህይወት ለሚኖረው የትዳር ጓደኛ ዳግም የማግባት ፈቃድ ለማስገኘት፣

### 2.3 የጋብቻ ኩነት ምዝገባ ጠቀሜታዎች

- ጋብቻው ህጋዊ መሆኑን ለማረጋገጥ፣
- የተጋቢዎቹን ዝምድናና ግንኙነት ህጋዊነት ለማረጋገጥ፣
- የጋብቻው ውጤት ለሆኑ ህጻናት በቤተሰብ የመጠበቅ ህጋዊ መብትን ለማረጋገጥ፣
- ህጋዊ ወራሽነትን ለማረጋገጥ፣
- ጋብቻ በሚፈርስበት ጊዜ የልጆች አስተዳደግን ለመወሰን፣
- ወደ ውጭ ሀገር ለመጓጓዝ ፓስፖርት የማግኘት ፈቃድን ለማቅረብ፣
- የልጆችን ህጋዊነት ለማረጋገጥ፣



### 2.4 የፍቺ ኩነት ምዝገባ ጠቀሜታዎች

- ፍቺ ለመፈፀሙ ህጋዊ ማረጋገጫ ለመሆን፣
- ለተፋቺዎች እንደገና የማግባት መብት ለማስገኘት፣
- ከፍቺ በኋላ የንብረት ክፍፍል ለማድረግ፣
- ከፍቺ በኋላ ስለተወለዱ ልጆች ህጋዊ መረጃ ለማግኘት፣
- ከፍቺ በኋላ በአንደኛቸው ላይ ከሚመጡ የገንዘብ ወይም የንብረት ጥያቄዎች (ዕዳ) ነፃ ለመሆን፣

### 2.5 በሃገር አቀፍ ደረጃ የሚያስገኘው ጠቀሜታ

- ቀልጣፋና ውጤታማ የፍትህ ስረአት ለማስፈን፤
- አስተማማኝ የስነህዝብና የጤና ስታትስቲክስ ለማስገኘት፤
- ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶችን ፍትሃዊ ለማድረግ፣

## 3. ወሳኝ ኩነቶች የት ማስመዝገብ ይቻላል

**3.1 የልደት ምዝገባ ቦታ፡-** ባስመዝጋቢው መደበኛ መኖሪያ ቦታ አቅራቢያ በሚገኝ አስተዳደር ጽ/ቤት (ቀበሌ) ይሆናል።

**3.2 የጋብቻ ምዝገባ ቦታ፡-** ተጋቢዎች በጋራ ለመኖር የሚወስኑት ቦታ ፤ ከተጋቢዎቹ አንዱ ይኖርበት የነበረው ቦታ ወይም ከተጋቢዎቹ የአንደኛው ወላጆች ወይም የቅርብ ዘመዶች የሚኖሩበት መደበኛ መኖሪያ ቦታ (ቀበሌ) ይሆናል።

**3.3 የፍቺ ምዝገባ ቦታ፡-**

- ፍቺው የተፈጸመበት ፍ/ቤት አቅራቢ በሚገኝ አስተዳደር ጽ/ቤት ወይም በተፋቺዎች መደበኛ መኖሪያ ቦታ በሚገኝ አስተዳደር ጽ/ቤት (ቀበሌ) ይሆናል።

**3.4 የሞት ምዝገባ ቦታ፡-**

- የሞት ምዝገባ ቦታ በሟች መደበኛ መኖሪያ ቦታ አቅራቢያ በሚገኝ የአስተዳደር ጽ/ቤት (ቀበሌ) ይሆናል
- ማንነቱ ወይም መደበኛ መኖሪያ ቦታው ለማይታወቅ ሟች የሞት ምዝገባ ቦታ አስክሬኑ በተገኘበት ቦታ አቅራቢያ በሚገኝ የአስተዳደር ጽ/ቤት (ቀበሌ) ይሆናል።
- በአዳሪ ት/ቤት ወይም በሌላ የጋራ መኖሪያ ቦታ የሚፈጸም የሞት ምዝገባ ቦታ በአስመዝጋቢው ተቋም አቅራቢያ በሚገኝ የአስተዳደር ጽ/ቤት (ቀበሌ) ይሆናል።